# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**:- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ጥር 14 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**-ወጣቱ በጥምቀት በዓል ላይ ህብረት በመፍጠሩ ወያኔን አስደነገጠ፤**

**-በጎንደር ሰዎች ሲታሰሩና ሲዋከቡ እንደነበር ተጋለጠ፤**

**-ወያኔ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ሊያደራጅ የያዘው እቅድ ውድቅ ሆነበት፤**

ዘወትር በብጥብጥ እና በትርምስ ተጀምሮ እንዲያልቅ ሲለምኑና ሲማፀኑ የኖሩት የወያኔው አባል አባ ገብረ መድህን በዘንድሮው የጥምቀት በዓል ላይ ለየት ያለ ክብር አግኝቼ በደመቀና ባማረ ሁኔታ አክብሬ እውላለሁ ብለው ያሰቡት ባለመሳካቱ አኩርፈው እንደነበር ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገለፁ::

በአለቃቸው መለስ ዜናዊ ትዕዛዝ በሰው ልጆች ደም እጃቸውን ያጨቀዩ የደርግ ባለስልጣናትን በብሔራዊ እርቅ ስም ለማስፈታት ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩት አባ ገብረመድህን ያሰቡት ሳይሳካ በመቅረቱ ከመቼውም ግዜ በላይ በጥምቀት በዓሉ ላይ ተከፍተው እንደነበር ተገልጾዋል::

በየአብያተ ክርስቲያናቱ እና ገዳማቱ ባህታውያኖችን በጥይት ግንባራቸውን ሲያስነድሉ የኖሩት አባ ገብረ መድህን በዘንድሮው የጥምቀት በዓል ላይ የተለየ ታሪክ ሰራሁ ብለው ተኮፍሰው ሊያከብሩ አቅደው የነበረ ቢሆንም የሰማእታቱ ቤተሰቦች እና የደርግ ሰለባ ዜጎች ባሰሙት ተቃውሞ እቅዳቸው ባለመሳካቱ አኩርፈው በቀዘቀዘ ስሜት በግድ እንዳከበሩ የገለጹት ቅርበት ያላቸው ወገኖች በአንጻሩ ችግር እና መከራ እየተፈራረቀበት ያለው ህዝብ ለሀይማኖቱና ለባህሉ ባለው ከፍተኛ ክብር ምክንያት እጅግ በደመቀ ሁኔታ አክብሮ መዋሉ ታውቆዋል::

በመላ ሀገሪቱ በብሔራዊ ደረጃ የሚከበረው የክርስትና እምነት ተከታዮች በዓል የሆነው የጥምቀት በዓል እጅግ በተለየ ሁኔታ ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ያከበረ ቢሆንም ጭር ሲል አልወድም የሚለው የወያኔ ቡድን ግን ህዝቡን በመፍራት በሲቪል ደህንነቶች እና በፖሊስ ወጥሮ ያሳለፈው በውስጡ የፈጠረው ፍርሀት መሆኑ ታውቆዋል።

በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ አድባራት የከተራ ዕለት ማክሰኞ ጥር 10 ቀን 2003 ዓ.ም እና የጥምቀት ዕለት ረቡዕ ጥር 11 ቀን 2003 ዓ.ም ታቦት ወደ ማደሪያቸው ባደረጉት ጉዞ እና ሲመለሱም እስከ ዛሬ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ምንጣፍ አንጥፈው .....ቄጠማ ጎዝጉዘው ......በባንዲራ መንገዶች አሸብርቀው ያከበሩ ሲሆን በአንጻሩ የወጣቱ ተሳትፎና ጨዋነት የወያኔን አንጀት ያቃጠለ እንደነበር አስረግጦ ያለፈ በዓል ሆኖዋል።

ወጣቱን ባህሉን አጉዳፊ በሆኑ ፊልሞች መርዞና በተለያዩ ሱሶች እንዲጠመድ አድርጎ እንዳሻው ሊጋልበው ሲያመቻች የነበረው ወያኔ ባሰበው መንገድ ሳይሆን በተቃራኒው ባህሉን እና ሀይማኖቱን አክባሪ ሀገር እና ህዝብ ወዳድ በመሆን ያለ አንዳች ግፊት በራሳቸው አስተባባሪነት በዓሉን አድምቀው ሲያከብሩ ከማዋላቸውም በላይ ለጥበቃ ተብሎ የተበተኑትን ፖሊሶች ሳያስታውስ ከራሱ በተውጣጡት ህግ አስከባሪ እጅግ ወደር የሌለው በዓል ሆኖ እንዲከበር ማድረጉ የወጣቱ ትብብር ዘልቆ መሄዱን ያረጋገጠ እና በሌላ ጎኑ ደግሞ የወያኔን ቡድን ያስደነገጠ እንደነበር ታውቆዋል።

ባህል እና ሀገር አፍራሽ ታሪክ በራዥ የሆነው የወያኔ ጨፍጫፊ ቡድን በአዲስ አበባ በተለያዩ መሸሽጊያ ቦታዎች ተወርዋሪ ፌዴራል ፖሊሶችን አስታጥቆ መትረየስ የተጠመዱ ፓትሮሎችን እና የአድማ መበተኛ መኪኖችን አዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም በበዓሉ ላይ ወጣቱና ህዝቡ እጅና ጓዋንት ሆኖ አንድም ህግ አስከባሪ ፖሊሶችን ሳይፈልግ በራሱ መንገድ ከማክበሩም በላይ የደከሙ እናት አባቶችን ደግፈውና አቀፈው ጥላ ስር በማስቀመጥ ብሎም ለስላሳ እየገዙ በመስጠት እስከ ዛሬ ድረስ ያልታየ የመከባበርና የመፈቃቀር ስሜት የታየበት ታሪክ በመስራቱ ወያኔ ከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ እንደወደቀ ለማወቅ ተችሎዋል።

አንዱን ብሔር ከሌላው..... ሙስሊሙን ከክርስቲያኑ......ገጠሬውን ከከተሜው እየነጣጠለ እና እያጋጨ የራሱን ስልጣን እድሜ ሲያራዝም የኖረው ዘረኛው የወያኔ ቡድን ዘንድሮም እሱ በቀደደው መንገድ ወጣቱ ይገባል ብሎ ሲጠብቅ የነበረ ቢሆንም ያሰበው ሳይሳካ...... የተመኘው ሳይሆን....... የጸለየው ሳይሰራ...... ይልቁንም በተቃራኒው አንድ ህዝብ ሆኖ ችግሩን ችግሬ ደስታው ደስታዬ ብሎ ሁሉም በአንድነት ያከበረበት እና አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት ዕለት እንደነበር የተዘዋዋሪ ሪፖርተራችን ዘገባ ያስረዳል።

የኑሮ ውድነቱ መሸከም ከሚችለው በላይ ቢሆንም እርስ በእርስ ተደጋግፎና ተፋቅሮ አንተ ትብስ አንቺ እየተባባለ ያከበረ ከመሆኑም በተጨማሪ ህግ ሊያስከብሩ ሳይሆን ሁከት ሊፈጥሩ የመጡ የደህንነት አባሎች እና የፌዴራል ፖሊሶች በስነ ስርዓቱ ላይ የተገኙ ቢሆንም ወጣት አዛውንቱ ለባህሉና ለሀይማኖቱ ተገዥ በመሆን እራሱ አስከባሪ እራሱ የፕሮግራሙ መሪ እራሱ ፈጻሚ ሆኖ ኢትዮጵያዊነቱን ያስመሰከረበት ዕለት ነበር።

አባ ገብረመድህን የአለቃቸውን የመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ እና ከውድቀት አድኑኝ ልመና ተግባራዊ ለማድረግና ለማሳካት  ሁለት ወራት ያህል ሲሮጡ የቆዩ ቢሆንም ዳር ደረሰ ብለው መግለጫ ሲሰጡ ሲፈርስ ተሳካ ብለው ሲናገሩ ሲናድ ያሰቡት ሳይሆን በመቅረቱ በብስጭት ሀዘን በተሞላበት ስሜት ቀዝቅዞዋቸው ነበር በዓሉን ያሳለፉት::

የወያኔ የስልጣን እድሜ እንዲራዘም እና እንዲቀጥል ብሎም ዘላለማዊ እንዲሆን ምን ግዜም እየሰሩ ያሉት እኚሁ የእምነት አባት ነኝ ባይ ቀልደኛ አዛውንት በደረሰባቸው የፖለቲካ ኪሳራ በመበሳጨት ፕሮግራሙን አጭር አድርገው ለመበተን ከአንድም ሁለት ሶስት ግዜ ሙከራ አድርገው የነበረ ቢሆንም ህዝቡና ካህናቱ በጀመሩት ፕሮግራም በመቀጠላቸው በንዴት ላይ ብስጭት ሆኖባቸው በተቀመጡበት እንቅልፋቸውን ሲያስነኩት በካሜራ ተቀርፆ በቀጥታ ስርጭት  ሊተላለፍ ችሎዋል::

ልክ የዛሬ አምስት ዓመት  በዚሁ በጥምቀት በዓል ላይ በጃን ሜዳ ወጣቱ የኢትዮጵያን ባንዲራ አንግቦ ወያኔ ይውደም ኢትዮጵያ ትቅደም! እያለ ተቃውሞ በሚያሰማበት ወቅት አልሞ ተኩዋሽ ቅልብ የቤተ መንግስት ወታደሮች እና የፌዴራል ፖሊሶች አንድ ላይ በመሆን በመትረየስ እና በስናይፐር ስንቱን ሜዳ ላይ እንዳስቀሩት የሚታወስ ነው::

ዘንድሮም የለመዱት የሰው ልጆች ደም ማፍሰስ ግብራቸው ቀርቶባቸው አንዴ በፌዴራል ፖሊስ ሌላ ግዜ በደህንነት ሰራተኞቻቸው ህዝቡን ለመበጥበጥ ቢሞክሩም ትዕግስትን የተላበሰው የበዓሉ ታዳሚ ግን በወጣት አስተናጋጆች እየተመከረ በዓሉን አክብሮ ውሎዋል::

ዛሬ ያለ ምንም ሐጢያታቸው የታሰሩ እና የተረሱ ዜጎችን  በይቅርታም ሆነ በምህረት ማስፈታት ትተው እንደ ወያኔው  መሪዎች በህዝብ ደም እጃቸው የጨቀየውን የደርግ ባለስልጣናትን አስፈትተው ብሔራዊ እርቅ አወረድኩ ብለው ሊፎክሩ ተዘጋጅተው የነበሩት አባ ገብረመድህን ከሁሉም ሳይሆኑ ቀርተው ለብቻቸው ተንገዋለው በመቅረታቸው በዓሉን አደብዝዘው ለማለፍ ሙከራ ሲያደርጉ እንደነበር ተጋልጦዋል::

ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በጎንደር ከተማ የጥምቀት በዓል በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ የዋለ ቢሆንም ከህዝቡ ቁጥር ያልተናነሰ የደህንነት እና የፌዴራል ፖሊስ ተበትኖ የህዝቡን ነጻነት ሲፈታተን እንደዋለም ታውቆዋል::

በህዝብ እና በሀገር ላይ በሚሰራው ደባ እና ሴራ እየባነነ እና እየደነገጠ የሚገኘው የወያኔ አረመኔና ዘረኛ ቡድን ህዝብ ለበዓልም ሆነ ለክብረ በዓል ሲሰባሰብ አደጋ ያደርስብኛል የሚል ጭንቀት ውስጥ በመግባቱ በመሳሪያና በደህንነት ኃይሎች የህዝቡን የመንቀሳቀስ ነጻነት እየገደበ አልፎ ተርፎ የአይንህ ቀለም አላማረኝም በሚል የፈለገውን ሰው እየለቀመ ሲወስድ እንደነበር ከጎንደር የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

ከውጭ ሀገር የመጡ ሁለት የጎንደር ተወላጆች ጥቅምት 10 ቀን 2003 ዓ.ም የከተራ ዕለት የኢትዮጵያን ባንዲራ ሙሉ ልብስ አሰፍተው ለብሰው በበዓሉ ላይ የተገኙ ቢሆንም ያሰፋችሁት ልብስ የኮከብ ምልክት ስለሌለው ህገ ወጥ ተግባር ላይ ተሰማርታችሁዋል ሌላም ተልዕኮ ሊኖራችሁ ስለሚችል ለጥያቄ ትፈለጋላችሁ ብለው የደህንነት ሰራተኞች እንደ ወሰዱዋቸውና በዕለቱም ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዳልተመለሱ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

የኢትዮጵያን ባንዲራ ለምን ለበሳችሁ ተብለው ለብዙ ዓመታት ከሀገር ውጭ ኖረው የመጡትን ኢትዮጵያውያኖች ለእስር መዳረጋቸውና ማሰቃየታቸው በእጅጉ የሚያሳፍር ከመሆኑም በላይ ህዝቡ ባህሉን እና ክብሩን ጠብቆ በማክበሩ ያበገናቸው ወያኔዎች የበዓሉን መልክ ለመቀየር ሙከራ ሲያደርጉ እንደነበርም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::ማክሰኞ ዕለት የተያዙት ሁለቱ ኢትዮጵያውያኖች ለ24 ሰዓት ያህል ታስረው ባቀረቡት ፓስፖርት ሊፈቱ እንደቻሉም ለማወቅ ተችሎዋል::

በጎንደር የካርኒቫል በዓል ይከበራል በሚል በአሜሪካ 54ቱም ስቴት «ዲቪ ጎንደር 2003» በሚል ፖስተር ተዘጋጅቶና ተበትኖ የነበረ ቢሆንም ኢትዮጵያውያኖችም ሆነ የውጭ ሀገር ዜጎች አለመምጣታቸው ተረጋግጦዋል::

በሌላ ዜና የወያኔው ጳጳስ አባ ገብረ መድህን የሽምግልናው ጉዳይ ሳይሳካ እየበገኑ ባለበት በዚህ ወቅት ከወያኔ ተላላኪ ከእንድርያስ እሸቴ ጋር በመጋጨታቸው ማስፈራሪያና ማስጠንቀቂያ እንደደረሳቸው ታወቀ::

ሁለቱ የወያኔ የጀርባ አጥንቶች የሆኑት ግለሰቦች የተጋጩት የገና በዓልን ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ በዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚገኙ የክርስትና እምነት ተከታይ ተማሪዎች በዓላቸውን የሚያከብሩ ቢሆንም ዘንድሮ አይቻልም በሚል የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት እና የመለስ ልዩ አሸክሹዋኪ የሆነው ግለሰብ በመከልከሉ የተነሳ መሆኑ ታውቆዋል::

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በወያኔ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ በቤተ-መንግስት ቅልብ ጦር በመትረየስ እንደ ሳር ሲታጨዱ የተረፉት መድረሻ አጥተው ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ብለው አባ ገብረ መድህን መኖሪያ ቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያን ግቢ ገብተው አስጥሉን ሲሉ ማን በጥብጡ አላችሁ አርፋችሁ አትቀመጡም ነበር በማለት ከማስጣል ይልቅ ከግቢ እንዲወጡና በአውላላ ሜዳ ላይ በብዙ መቶ ተማሪዎች እንዲገደሉ ያስደረጉት እኚሁ ግለሰብ ዛሬ በእርቁና ሌሎች የተሰጣቸው የቤት ስራዎች እየወደቁና ለኪሳራ ስለዳረጉዋቸው ከመለስ ያጡትን ክብር በተማሪዎች ጀርባ ታክከው ለማግኘ ት ሙከራ ቢያደርጉም በማስፈራሪያና በማስጠንቀቂያ የጀመሩት ጥያቄ ውድቅ ሊሆን እንደቻለ ታውቆዋል::

ሁለቱ የወያኔ ቡድን ቀንደኛ አራማጅ ግለሰቦች የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ ተጋጩ ይባል እንጂ ተማሪዎቹ ያቀረቡትን ጥያቄና በደረሰባቸው ጉዳት ዙሪያ የጠለቀ አንዳችም ነገር ሳይኖር ለክብራቸውና ለመለስ ያለን ታማኝነት ብሎም ተደማጭነት የማን ይበልጣል ከሚል ፉክክር የተነሳ መሆኑን ጉዳዩን የሚከታተሉ ወገኖች ገልጸዋል::

በዓሉን እናከብራለን መብታችን ነው ብለው ከነበሩት  የክርስትና እምነት ተከታይ ተማሪዎች መሀከል አስተባባሪ ናቸው ተብለው ከ200 በላይ ታፍሰው ከሚኖሩበት አራት ኪሎ የኒቨርስቲ ግቢ ሲወሰዱ አንዳችም ትንፍሽ ያላሉት እኚሁ አባ ገብረመድህን ለማስመሰል  ሲሉ ብቻ ደብዳቤ ጽፈው ተማሪዎቹ በዓላቸውን ማክበር ይችላሉ ቢሉም እንድርያስ ግን አርፈህ ተቀመጥ ብሎ ምላሽ ሰጥቶ እንዳስፈራራቸው ታውቆዋል::

ከወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እኩል የህዝብ ጥላቻ ያለባቸው እነዚሁ ሁለት የወያኔ አጨብጫቢ ግለሳቦች ያጡትን ድጋፍ ለማሰባሰብ እና ብሎም የመለስን ታዛዥነት ለማረጋገጥ ያደረጉት እና የወሰዱት እርምጃ እንጂ ለተማሪዎቹ የሚጠቅም አለመሆኑን ታስረው የተፈቱ ተማሪዎች አስታውቀዋል::

ወጣቱ ሀገራዊ ስሜት እንዳይኖረው በዘር እና በጎሳ እየከፋፈሉ እርስ በርስ እያናከሱ ያሉት እነ እንድርያስ እሸቱ ተማሪዎች ለምን እምነታቸውን ጠብቀው ተጉዋዙ በሚል የክርስትና እምነት ተከታይ ተማሪዎች ቢከለክሉም በግቢ ውስጥ በብሄር እና በጎጥ  እንዲደራጁ ግን የገንዘብ እና የቁሳቁስ ድጋፍ እያደረጉ መሆኑ ታውቆዋል::

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ የሆኑ ተማሪዎችን በኦህዴድ ስር ለማደራጀት እና ከወዲሁ ለማጥመቅ ትልቅ ጉባዔ ቢጠራም በተጋባዥ እንግዶች እና በተማሪዎቹ መቅረት ሳይሳካ ቀርቶዋል::

አትሌት ደራርቱ ቱሉ ፤ድምፃዊ አሊ ቢራ ፤ድምጻዊ ቀመር ዩሱፍ ፤የአምቦ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ምትኩ ቲሶ፤በሽግግር መንግስቱ ግዜ የኦነግ ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረው ዘገየ አስፋው ፤የሪፍት ቫሊ ዩኒቨርሰቲ ባለቤት ድንቁ ደያስ እና ሌሎች ታዋቂ ግለሰቦች በዚሁ በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ በተዘጋጀው ጉባዔ ላይ ተጋባዥ እንግዳ ሆነው የተጠሩ ቢሆንም አንዳቸውም ሳይገኙ ከመቅረታቸውም በተጨማሪ ተማሪዎቹም እንደቀሩና ፕሮግራሙ እንደተሰረዘ ለመረዳት ተችሎዋል::

ወያኔ ኢትዮጵያዊነት ከወጣቱና ከተማሪው አዕምሮ ውስጥ ተሰርዞ እንዲጠፋ ለማድረግ እና ለአገዛዙ እንዲያመቸው በብሔር እና በጎጥ እየከፋፈለ እያደራጀ ሲሆን ሰሞኑንም የኦሮሞ ተወላጅ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን በቡድንተኛነት ሊያጠምቅ የነበረው እቅድ እንደከሸፈበት ታውቆዋል::

እራሱ ወያኔ እያወደመና እያጠፋ ያለውን ሀገር አካባቢያችንን እናልማ በሚል የውሸት ቃል በኦሮሞ ልማት ማህበር ስም ወጣቱን ከወዲሁ ሊያጠምቅ አቅዶት የነበረ ቢሆንም ያሰበው ሳይሳካ በመቅረቱ ፕሮግራሙን ያዘጋጁት የወያኔ ሹመኛ ካድሬዎች በብስጭት በተጋባዥ እንግዶቹ ላይ ስልክ እየደወሉ ሲያስፈራሩዋቸው እንደነበር ታውቆዋል::